# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ <u>ከዚኽ ወዴት?</u>

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***<u>ክፍል ስምንት</u>** <u>(ከክፍል ሰባት የቀጠለ)፤-..</u>*

በውሳኔው መሠረት ጉባዔ አዘጋጁ ክፍል ስለዚኽ አገር-አቀፍ ጉባዔ ዓላማና አስፈላጊነት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለኢትዮጵያውያንና ለዓለም-አቀፍ ኅብረተሰብ በጥናት ላይ የተመሠረቱ ቅስቀሳዎችና ገለፃዎችን በማድረግ፣ በጉባዔው አዘጋጅ አካል አባላት መኻል ልዩነቶችን ለመፍጠርና ለመከፋፈል እንዲሁም ከየአቅጣጫው እያንዳንዱ እቅድ እንዲሰናከል የተደረጉ እኩይ ጥረቶችን በአግባቡ በመቋቋምና በሽግግር መንግሥቱ ባለሥልጣናት የተደቀኑ መሰናክሎችን በመወጣት፣ ከአገር ውጭም ይሁን በአገር ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክና የሙያ ስብስቦች፣ ታዋቂ ግለ-ሰቦችና የልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍል ተወካዮች ተሣታፊ የሆኑበት ሁሉን-አቀፍ አገራዊ የሰላምና የእርቅ ጉባዔ ከታኅሣስ ፱ እስከ ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም አዲስ አበባ ላይ እንዲካሄድ ሙሉ ዝግጅቱን ማጠናቀቅና ተግባራዊ ማድረግ ቻለ።

በአገሪቱ ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ የሚገኙ የሽግግር መንግሥቱ ደጋፊም ሆኑ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች እና የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚወክሉ ስብስቦችና ማኅበራት ሁሉ ጉባዔውን እንዲደግፉና በዚኽ ጉባዔ ላይ ተገኝተው ቀጥታ ተሣታፊ እንዲሆኑ አዘጋጅ አካሉ ይፋዊና ቀጥተኛ ጥሪውን አስቀድሞ በተደጋጋሚ በማቅረቡ፤ ጉባዔውን ለመደገፍም ሆነ ተካፋይ ለመሆን ከኢሕአዴግ በስተቀር በ"ሽግግር" መንግሥቱ ውስጥ አባል የነበሩ ሳይቀር ከሞላ ጎደል ሁሉም አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል ማለት ይቻላል። ያም በመሆኑ አርባ-አምስት ድርጅቶች የጉባዔው ተሣታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።

ይኽ ሁሉም ኃይሎች በስፋት የተካፈሉበት ታሪካዊ ጉባዔ የተጠራው አንዳንዶች እንደሚሉት ሽግግር መንግሥት አቋቁሞ (መሥርቶ) ለመውጣት ሣይሆን አዲስ የሽግግር ሂደትን በመከተል፣ ሕዝባችን የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆንና የአምባ-ገነኖች በጉልበት ሥልጣን የመቀማማትና የቅብብሎሽ አዙሪት ተሰብሮ ሁሉም አቸናፊና ተጠቃሚ የሚሆንበት አዲስ ሕዝባዊ ሥርዓት በአገራችን እውን የሚሆንበትን ብሔራዊ-መግባባት-አስገኝ ዘዴና መንገድ <u>በምክክር ለመቀየስ የሚያስችል ውጤት</u> ይዞ ለመውጣት ነበር። የጉባዔው እምነትም፣ ትልምም ሆነ ትኩረት በሚገባ የማይተዋወቁ ኃይሎች በአንድ ስብሰባ ላይ ተገናኝተው በሚደርሱበት ጊዜያዊ ግኝትም ሆነ በሚያቋቁሙት ተቋም ላይ ሣይሆን የትግሉ ልዕለ-ግብ የጠራ <u>ሂደት</u> ላይ እንዲመሠረት በማድረግ ተግባር ላይ ያነጣጠረ ነበር።

ለዚኽም የሂደት ግብ እውን መሆን ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ጉባዔው በአምስት የመወያያ ነጥቦች (አጀንዳዎች) ላይ ትኩረቱን ሰጥቶ ተወያይቷል። እነሱም፡ ሽግግሩና ዴሞክራሲያዊ ሂደት፣ የሽግግሩ ወቅት የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች፣ የብሔር/ብሔረሰቦች መብትና የኢትዮጵያ አንድነት ልዕልና ጉዳይ፣ ሽግግሩና የሕገ-መንግሥት ጥያቄ እና የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች የትግል ትብብር ጥያቄ የሚሉ ናቸው።

ይኽ ለአምስት ቀናት የዘለቀ ጉባዔ በስድስት አንቀፆችና በአሥራ-ሦስት ንዑስ-አንቀፆች የተዘረዘሩ የጋራ ግንዛቤዎችን በመጨበጥ በአሥራ-ሁለት አንቀፆችና በአሥራ-ሁለት ንዑስ-አንቀፆች የተጠቃለሉ የጋራ የስምምነት ነጥቦችንና ውሳኔዎችን አስተላልፏል። ጉባዔው ዋነኛ ግብ አድርጎ የያዘውን *"የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን የሰላምና የዴሞክራሲ ፍላጎት ሊያሟላና የዓለም-አቀፍ ኅብረተሰብን አክብሮት ሊያገኝ የሚችለው አማራጭ የሁለት ዓመት ተኩሉ የሽግግር ወቅት በቻርተሩ መሠረት ሲያልቅ፣ ኢሕአዴግን ጨምሮ*

ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች የሚያቅፍ አዲስ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ማድረግ....” የሚለውን ዓላማ እውን እንዲሆን የደረሰባቸውን የስምምነት ነጥቦች ተግባራዊ እንዲያደርግ “የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት (ኢሰዴአኃ)” በሚል መጠሪያ ወደ-አምሣ የሚጠጉ በውጭና በውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችን በአባልነት ያቀፈ የትግል ድርጅት በማቋቋም ተቋጭቷል። ኢሰዴአኃ በአገር ውስጥ ሰላሣ-ሁለት፣ ከአገር ውጭ አሥራ-ስድስት ድርጅቶችን ያቀፈ ስብስብ ነበር። (*CAFPDE, Member Organizations.pdf)

ይኸ የፖለቲካና ፖለቲካዊ አደረጃጀት የሌላቸው ኃይሎች የተሣተፉበት አገር-አቀፍ የሰላምና እርቅ ጉባዔ እንደተጠናቀቀም በቀረቡት የመወያያ ነጥቦች ጉባዔተኛው የደረሰበት ድምዳሜ፣ ዓላማና እምነት “የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ሰነድ” በሚል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ ሆኗል።

በዚኸ ታሪካዊ ጉባዔ መክፈቻ ቀን (ታኅሣስ ፱ ቀን ፲፱፻፹፮ / December 18, 1993) ሠላሳ የውጭ አገር ኤምባሲዎች ተወካዮቻቸው በተጋባዥ እንግድነት እንዲገኙ አድርገዋል።*Embassy reps. at Ghion Congference in Addis, Dec. 18, 1993.pdf
ይኸ ለአምስት ቀናት በግዮን ሆቴል የተደረገ አገር-አቀፍ ጉባዔ በተሣካ ሁኔታ ለመከናወን የበቃው ከአገር ውጭና በአገር ውስጥ ያሉ አዘጋጅ አካላት አጠቃላይ የፖለቲካውን ይዘት፣ ሂደትና ዲካ በቅጡ በተረዱ እና የተወናገረውንና ፈር የለቀቀውን የኢሕአዴግ የሽግግር ሂደት የሚያስከትለውን ጦስ በተገነዘቡ ክፍሎች በመመራቱና በውጭና በውስጥ የሚደረገው ጥረት ግቡን እንዲመታ በሚያስደንቅ ቅንብርና ትጋት መሥራት በመቻላቸው ነበር።

የአቶ መለስ የሽግግር መንግሥትም ለማደናቀፍ ዙሪያ ጥምጥም ጥረት ቢያደርግም ጉባዔውን ከመደረግ ሊያስቀረው እንዳልቻለ ሲገነዘብ በዚኸ አገር-አቀፍ የሰላምና የእርቅ ስብሰባ ላይ ለመገኘት ከአገር-ውጭ የሚገኙ ድርጅቶችን ተወካዮች ከአዲስ አበባ አውሮጵላን ማረፊያ እየተቀበለ ቀጥታ እስር ቤት መወርወርን ምርጫው አደረገ። ይኸ አረመኔአዊ አድራጎትም እነኝኸ ተወካዮች ቢገቡ ተቃውሞ እንደማይገጥማቸው በአዲሶቹ ገዥዎች ቃል ተገብቶልናል ብለው “ማረጋገጫ” የሰጡና በመለስ ዜናዊ የሚመራውን ቡድን ከተካው ከደርግ በማነፃፀር ብቻ የሌለውን ዴሞክራሲያዊ ባኅሪይ ሊለግሱት የሚግደረደሩትን የውጭ ደጋፊዎቹን ግር ያሰኘና ያስደነገጠ፣ በአገራችን ከአዲሶቹ ገዥዎች ያጨነቆረ ጠባብ እይታ ውጭ እውነተኛ የሰላምና የእርቅ ሂደትን የተከተለ ብሔራዊ-መግባባት ላይ የተመሠረተ የሥርዓት ለውጥ እንዳይኖር በሩ ጥርቅም ብሎ እንደተዘጋ እና አምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓት በአዲስ ዘይቤ ለመደላደል በቁርጠኝነት እንደተጀመረ የማያወላዳ መልእክትን ያስተላለፈ እብሪታዊ እርምጃ ነበር።

የኢትዮጵያ የሰላምና የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት (አማራጭ ኃይሎች) ከላይ በተጠቀሰው ሁኔታና መንፈስ ከኢሕአዴግ ሙሉ ቁጥጥር ውጭ የነበሩና በወቅቱ አሉ የተባሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ስብስቦችን አቅፎና በሠፊ መሠረት ላይ ቆሞ በአዲስ የሽግግር ሂደት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገራችን እውን እንዲሆን ለአዲስ የእርቅና የሰላም ጅማሮ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት መዋቅሩን ዘርግቶ እንቅስቃሴ አደረገ። ሕዝቡም በኢሕአዴግ ይዞታ አለመደሰቱንና ለለውጥ ያለውን ፍላጎት፣ ጉጉትና ዝግጁነት ኢሰዴአኃ በተቋቋበት ጊዜ መልእክቱን አዲስ አበባ ላይ ባደረገው ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍና በልዩ ልዩ መልክ ገልጿል።

አማራጭ ኃይሎች የሚከተሉትን ውጤቶች ለማስመዝገብና ለማከናወን ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

- በውጭም ሆነ በውስጥ ያለው ለውጥ ፈላጊ ክፍል በአንድ ድርጅት ጥላ (በአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት - ኢሰዴአኃ) ሥር መጠቃለል በመቻሉ ለጊዜውም ቢሆን ለሕዝባችን ተስፋ ሰጥቷል፣ የትግል ወኔውን ቀስቅሷል።
- ለተቃዋሚው ክፍል በውጭ ባዕዳን ኃይሎች ዘንድ ቀደም-ሲል ከነበረው የተሻለ ተደማጭነትና ከበሬታን ማትረፍ አስችሏል።
- ጉባዔውም ሆነ የእሱ ውጤት የሆነው አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት የፖለቲካ ድርጅቶችን ብቻ ሣይሆን በመስክ ላይ ያሉ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትንና ስብስቦችን የጨመረ በመሆኑ የለውጥ ፈላጊው ጎራ ሠፊ-መሠረት ያለው ጠንካራና ቁርጠኛ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚያስችለውን ሁኔታ መፍጠር ችሏል።
- በተለይ ወቅቱ የኢሕአዴግ የ"ሽግግር" ጊዜ በ"ቻርተሩ" መሠረት ጥር ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ/ም እንደሚያከትም ቢታወቅም ኢሕአዴግ ግን እራሱን ወደ ቋሚ መንግሥትነት ለመቀየር የሚያስፈልገውን ጥልፍል ማረጋገጫ ሰርቶ ያላጠናቀቀ በመሆኑ እንዳሻው ጊዜውን ለማራዘም የወሰነበት፣ የራሱን ደጋፊዎችና ጉዳይ አስፈፃሚዎች በሕገ-መንግሥት አርቃቂ ስም አቋቁሞ የድርጅቱን የፖለቲካ መርኃ-ግብር (ፕሮግራም) በአገር ሕገ-መንግሥት ስም ለማወጅ ሽር-ጉድ የሚልበት፤ (*1) በአኳያው በተለመደው ሕዝብን በናቀ የማን-አለብኝ እብሪት የዜጎችን መብት በመጣስ፣ በመሰሪ ተንኮል የተለያዩ ሰበቦችን እየፈጠረ ለዝንታለም የቆየን የሕዝብ ትስስር በማደፍረስ እርስ-በርሱ እንዲናቆር ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ ይጣደፍ የነበረበት ጊዜ ስለነበር፣ ኢሰዴአኃ እያንዳንዱን ነጥብ በመቃወምና አማራጮቹን በማሣየት ለጊዜው ለኢሕአዴግ የልብ ውጋት፣ አስተማማኝ ሰላምና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለጠማውና ለውጥ ለፈለገው ክፍል አለኝታ፣ የሕዝብ ልሣን ለመሆንና የዜጎችን አመኔታ ለማትረፍ ችሏል። (የደቡብ
- ኢሰዴአኃ በተቋቋመበት መንፈስ በአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረቱን አሳርፎ ለሕዝብ ተስፋ ሰጭና ለጋራ ትግል ቀስቃሽ የሆኑ "ለአዲስ ዴሞክራሲያዊ ጅማሮ" የመሣሰሉትን ጥናታዊ ሰነዶችና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጽሑፎችን "አማራጭ" በተሰኘው ልሣኑና በልዩ ልዩ በራሪዎች አማካይነት በማሰራጨትና ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በማድረግ ችግሮች የት ላይ እንዳሉና መፍትኄውም በተባባረ የጋራ ትግል እውን ለሚሆን አዲስ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ሂደት እንደሆነ ያላሰለሰ ትግል አድርጓል።
- በውጭ ቀጥታ አባል ከሆኑና አባል ካልሆኑም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሙያ ስብስቦችና ደጋፊዎች የተውጣጡ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶችን በማቋቋም የጋራ ትግሉ በተሰባሰበ መልክ እንዲቀጥል፣ የዲፕሎማሲው ሥራ ወጥ-በሆነና ቅጥ-ባለው መንገድ እንዲካሄድ፣ ልዩ ልዩ እርዳታዎች በአገር ውስጥ ለሚደረገው ትግል እንዲደርሱ፣ ወዘተ፣.. ማድረግ አስችሏል፤ (በዚኸ ረገድ በተለይ በሰሜን አሜሪካው የኢሰዴአኃ ም/ቤት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አማካይነት ኢትዮጵያውያን ስለ ኢሰዴአኃ የተሻለ እንዲያውቁ፣ ቢያሉበት እየተደራጁና ንዑስ አካሎችን እያቋቋሙ የትግሉ ተሣታፊ እንዲሆኑና በሁሉም ዘርፍ እርዳታቸውን እንዳያቋርጡ፣ አባል ያልሆኑ ድርጅቶች ኢሰዴአኃን እንዲቀላቀሉ፣ አባል የሆኑት አንዳንድ ልዩነቶችን አቻችለውና ከዋናው ጽሕፈት ቤት ጋር የነበሩ የአሠራርና የአካሄድ ችግሮችን ታግሰው በጋራው መሥመር እንዲቆዩና በተቻለ መጠን ተቃዋሚው ጎራ በአንድ ድምፅ እንዲናገር፣ ሰነዶችን በማዘጋጀት የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚመለከታቸውና በኢሕአዴግ ላይ ጫና በማድረግም ይሁን ለዴሞክራሲያዊ ሂደቱ መልክ መያዝ ለሚደረገው ሕዝባዊና ሰላማዊ ትግል አስተዋፅዖ የሚኖራቸውን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ክፍሎችና ተቋማት በአካል ጭምር በመገናኘት የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ እንዲገነዘቡና ለኢሰዴአኃ የዲፕሎማሲ ድጋፍ እንዲለግሱ፣ ወዘተ.. ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በአውሮጳም እንዲሁ በኢሰዴአኃ ቅርንጫፎች አማካይነት ተመሣሣይ ጥረቶች ተደርገዋል።)

- ለአዲሶቹ ገዥዎች ተቃዋሚ ማለት የእነሱን መሥመር የሚከተልና ትእዛዝ-ፈጻሚ ብቻ እንደሆነና የሥልጣን ተቀናቃኝ ሊሆኑ ከሚችሉና ሕዝብ አመኔታውን ከሰጣቸውም ይሁን ሠፊ መሠረት ካላቸው ክፍሎች ጋር በግልፅ ለመነጋገርና ለመደራደር ምንም ፍላጎት እንደሌለው ከኢዴኃቅ ጀምሮ ቀደም-ሲል ከነበሩ የተቃዋሚው ስብስቦች የቀረቡ ቀና ጥሪዎችን በመናቅ አደናቃፊና አፍራሽ ሚናን ከመጫዎት ውጭ ምንም ዓይነት አዎንታዊ ምላሽ እንዳልሰጠ ሁሉ፣ ኢሰዴአኃ ላቀረባቸው በጎ ጥሪዎችም የነበረው አቋም የተለየ አልነበረም። ለአዲሶቹ ገዥዎች ተቃዋሚ ማለት፣ በአቶ ዳዊት ዮሐንስ በወቅቱ የአገዛዙ አፈ-ቀላጤ አባባል "እራሣቸውን የሚያዩበት መስታወት" እንደሆነና የእነሱን መሥመር የሚከተልና ትእዛዝ-ፈጻሚ ብቻ ከመሆን ውጭ ለአገርና ለሕዝብ አማራጭ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል ተደርጎ አይወሰድም። ይኸ ደግሞ የ"አብዮታዊ ዴሞክራሲ" እምነታቸው አካል ስለሆነ ኢሰዴአኃንም ያዩትና የፈረጁት ለእነሱ አማራጭ ሆኖ ለሕዝብ እንደሚቀርብ አካል ሣይሆን እንደ ጠላት ነበር። በመሆኑም ኢሰዴአኃ ለተወሰ ጊዜም ይሁን እንጂ በውጭም ሆነ በውስጥ ያሉትን ኃይሎች አስተባብሮ ሕዝባዊና ሰላማዊ ትግሉን በተቀናበረ መንገድ ለማስኬድ ጥሩ ጅማሮ ላይ በመሆኑና ከሽግግር መንግሥቱም ጋር ለመደራደርና አዲስ ሂደትን በጋራ ለመጀመር ዝግጁነቱን በድፍረት ማሳወቁና ኳሱን "የረባ ተቃዋሚ የለም" እያሉ ማፌዝን ዘይቤ ወደ-አደረጉት የኢሕአዴግ መሪዎች መወርወርና ምላሽ-ሰጭ ማድረግ ችሏል። በኢሕአዴግ መሪዎች በኩል ግን በዓለም ላይ ያለ የሌለ ሰበብ አስባብ እየደረደሩ የቀረበላቸውን የሰላም ጥሪ አሻፈረኝ በማለትና ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ ለመደራደር ፈቃደኛ አለመሆናቸው፣ ከእውነተኛና ተአማኒነት ካላቸው ክፍሎች ጋር አብሮ ለመሥራት ፍላጎት እንደሌላቸውና የሚከተሉት ሂደት ከአሣታፊ ዴሞክራሲና ከመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት ጋር ምንም ትውውቅ የሌለው ፀረ-ዴሞክራሲና አምባ-ገነን እንደሆኑ በውጭ ደጋፊዎቻቸው ዘንድ ሣይቀር ይበልጥ እንዲጋለጡ አስችሏል። ኢሰዴአኃ በተከተለው የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴው የኢሕአዴግ መሪዎችን አምባ-ገነናዊ ባኅሪይ በጎላ መልኩ ለዓለም ማሳወቅ ችሏል።
- በውጭም ሆነ በውስጥ ያሉ ለውጥ ፈላጊ ኃይሎች አንድ ላይ ተባብረው በመሥራት በጥንቃቄና በተገቢ ከተያዙ ለሕዝባዊ ትግሉ ልዕለ-ግብ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሊያደርጉ የሚችሉ የተወሰኑ የአጭር ጊዜ ግቦችን መምታት እንደሚችሉ ኢሰዴአኃ አረጋግጧል። በተለያዩ እምነቶች ዙሪያ የተደራጁ ድርጅቶችም ለአገራዊና ሕዝባዊ ዓላማዎች እውን መሆን በጋራ ለሚያደርጉት ቀጣይ ትግል በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊነት ጎኖች የሚፈረጁና ትምሕርት-ሰጭ የሆኑ ልምዶችን አስገኝቷል። ኢሕአዴግም ተቃዋሚውን ጎራ በተመለከተ የሚከተለውን ስልት ለማስተካከል ከኢሰዴአኃ ጠቃሚ ትምሕርትን እንደቀሰመ መገመቱ አያዳግትም።

ይሁንናም ኢሰዴአኃ ከዚኽ በላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም ማከናወን ቢችልም፣ በውጭም ሆነ በውስጥ የሕዝብ ድጋፍ እጥረት ሳይኖርበት የተነሳበትን ዓላማ ለማሳካት አልተቻለውም። ለዚኽ ብዙ ምክንያቶች ሊደረደሩ ይችላሉ። ሆኖም የዚኽ ሕቶት ዓላማ ያለፉ የጋራ የትግል መድረኮችን ሂደትና ይዞታ ዞር ብሎ በአጭር በመጎብኘት ከነሱ ተመክሮ የሚቻለውን ያኽል ልምድ በመቅሰም የተሳሳትነውን አርመን መልካሙን አጎልበትን ቀጣዩ ሕዝባዊ ትግላችን የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችል ስለሆነ ኢሰዴአኃንም የምናየው ከዚሁ ማዕዘን ብቻ ይሆናል።

ኢሰዴአኃ ምክር ቤት በተመሠረተበት መንፈስ ተልዕኮውን ሙሉ በሙሉ ለማሳካት እንዳይችል ያደረጉትና ለውድቀት የዳረጉት እክሎች በአብዛኛው በሌሎቹም ተመሣሣይ ጥረቶች ላይ የታዩና ከዚያም ወዲኽ በተደረጉ የጋራ ትግል መድረኮች የቀጠሉ ችግሮች ናቸው ማለት ይቻላል። በአጭሩ የአወቃቀር፣ የትግል ትልምና የአመራር ችግሮች ሆነው እናገኛቸዋለን።

***በክፍል ዘጠኝ ይቀጥላል........***